የሰ/መ/ቁ. 39085

የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን - ነ/ፈጅ አቶ ዳንኤል ጥበቡ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- እነ ወ/ር አስረሳች ወርቅነህ (87 የጉምሩክ ፖሊሶች)

ጠበቃ ሙሉጌታ ወንድማገኝሁ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው የጉምሩክ ፖሊሶች ወደ ስራ እንመለስ የሚል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆኑ አመልካች ተከሳሽ ነበር፡፡ እሱም በድርጅቱ ከተራ ወታደርነት እስከ መኮንንነት ተመድበን ከምንሰራበት በማይታወቅ ሁኔታ ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ ያሰናበተን ከጉምሩክ ፖሊሶች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 4/96 ውጪ በመሆኑ ሕገ-ወጥ ነው እንዲባልና ወደ ስራ እንድንመለስ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለውም በጉምሩክ አዋጅ የመዋቀር ማስተካከያ በማድረግ የሰው ኃይል ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ ስልጣን ተሰጥቷል፡፡ መመሪያው የዲስፒሊን እርምጃን የሚመለከት እንጅ የመዋቅር ማስተካከልን የሚከለክል አይደለም በማለት ስንብቱ ሕጋዊ መሆኑን በማስመልከት የመቃወሚያና በአማራጭ የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ፍ/ቤት ወደ ቀድሞ ስራቸውና ደመወዛቸው እንዲመለስ ሲል ወስኗል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 64577 ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የመጀመሪያ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 7 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ መሰረት በማድረግ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን አለው ወይንስ የለውም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዝዞ ተጠሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ ተደረጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክር አካሄደዋል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የአመልካች ዋና ክርክር በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 8/2/መ እና በአዋጅ ቁጥር 368/1995 በተሻሻለው መሰረት የጉምሩክ ፖሊሶች የሚተዳደሩት የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በሚተዳደርበት አኳኋን ነው፡፡ በዚህ ዓይነት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ፍ/ቤት ማየቱ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ ለሚደርሰው የመብትና የፍትህ መጓደል አቤቱታ የሚቀርብበት በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል ባለመኖሩ መብትና ጥቅማችን የሚያስከብርና ሕጐችን በመተርጐም የሚወሰንልን መደበኛ ፍ/ቤት ብቻ ስለሆነ ክሱን ተቀብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአዋጁ ቁጥር 368/95 እንደተመለከተው የጉምሩክ ፖሊስ ኃይል የሚተዳደረው የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን አዋጅና ደንብ ተከትሎ በሚወጣው መመሪያ መሰረት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች በግልጽ ባልተመለከቱ ጉዳዮች ስንብት ቢፈፀም በፍ/ቤት እንደሚታይም አልተመለከቱም፡፡ የበታች ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው በመመሪያ ቁጥር 4/1996 ከተመለከተው የጉምሩክ ፖሊስ አገልገሎት ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ውጪ በሆነ ሁኔታ ከመዋቅር ማሻሻያ ጋር ተያይዞ ከመጣው የጉምሩክ ፖሊስ ኃይል አደረጃጀትን የሚመለከት ጉዳይ እንጂ

በመመሪያው ላይ ስለስንብት የተመለከተውን ምክንያት የሚሸር ባለመሆኑ ስንብቱ ከመመሪያው ውጪ ነው በማለት ነው፡፡ በመመሪያው ከተመለከቱ ምክንያቶችም ሆነ በመመሪያው ከተመለከቱ ምክንያቶች ውጪ የጉምሩክ ፖሊስ የስራ ስንብት ጉዳይ ሊታይ የሚችለው የፌዴራል ፖሊስ በሚተዳደረው ስርአት እንደሆነ በአዋጁ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ የጉምሩክ ፖሊሶች የስንብት፣በስራ ላይ ማስማራትም ሆነ የዲስፒሊን ውሳኔ ጉዳዮች በቀጥታም ሆነ በይግባኝ በፍ/ቤት በዳኝነት ሊታይ የሚችልበት ስርአት በአዋጅ ወይም በመመሪያው ባልተመለከተበት ስንብቱ ሕጋዊ ነው ወይንስ ከሕግ ውጪ ነው በማለት በፍ/ቤት ጭብጥ ተይዞ ክርክር ሊካሄድበትና ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

በመሆኑም የበታች ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ብቸኛ ስልጣን ያለው ፍ/ቤት ነው በማለት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስና ክርክር ተቀብሎ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው ወደ ስራ መልሷቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ በአዋጅ በግልጽ የፌዴራል ፖሊስ በሚተዳደረው ስርአት (executive provocative) የሚታየውን ጉዳይ ያለስልጣኑ ለጥጦ በመተርጉም በፍ/ቤት የሚታይ ጉዳይ በማድረግ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ማረም ሲገባው በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ከላይ በተመለከቱ ምክንያቶች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 98010 በ14/5/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64527 በ1/11/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጡ ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪዎች ወደ ስራ ሊመለሱም ሆነ ደመወዝ ሊከፈላቸው አይገባም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የቻቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ